# ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ!!

መልእክት ለአቶ አባኪያ

መቸም የዘንድሮዉ ፖለቲካ በግሩ ሳይሆን በራሱ መሄዱን እየተመለከትን ነዉ። ጆሮ አይሰማዉ ጉድ የለዉም ይሉ ነበር አበዉ ሲተርቱ፤ ትክክል ነዉ አሁንም ጆሮ መስማት የማይችለዉ ጉድ የለም። ሁሉም ቁም ነገር ባይሆንም ሰሞኑን ያነበብኩት ጉድ አልጥም ስላለኝ ነዉ ብቅ ያልኩት። አቶ ወይም ወይዘሮ ይሁኑ አላውቅኩም አባኪያ የተባሉ ጸሀፊ ኢትዮጵያ ዛሬ በተባለ ድህር ገጽ ላይ "በእውኑ ብርቱካን ከቴዎድሮስ ታንሳለችን ?! እውነት እውነት እላችኋለሁ፡ አታንስም ! !" በሚል ርእስ የጻፉትን ስመለከት ኢትዮጵያም ሆነ ራሳቸዉ ጸሀፊዉ ስላሳዘኑኝ ብቅ ልበልና ያቅሜን ልበል ብየ ነዉ ይህችን አጭር መልስ ለመስጠት የወሰንኩት። ኢትዮጵያ ሀቀኛ ልጆችዋ አለቁ መሰል ታሪኳን የማያዉቅ ወይም አዉቆ የሚያጣምም ብቅ እያሉ ለኢትዮጵያ ቀርቶ ለሰዉ ሲያድሩና ጀግኖቿን አቆሽሸዉ ከሃዲዎቹን ሲያሞጋግሱ ሳይ ለኢትዮጵያ አዘንኩ። ያላዋቂ ሳሚ ን.. ይለቀልቃል ኢንደሚባለዉ ሁሉ ታሪክን ሳይመረምሩ ጀግናን ከባንዳ ሳይለዩ በማወዳደርና ደካማን አጎለብታለሁ ብለዉ ከሃዲን አሞጋግሰዉ ህይዎታችዉን ለኢትዮጵያ ብለዉ የሰጡትን ዝቅ አድርገዉ ከዘመኑ ባንዳዎችም ያንሳሉ ብለዉ ሊያሳምኑን ለሞከሩት ጸሃፊዉም ታሪክ አለማወቃቸዉን ባለማዎቃቸዉ አዝኘላቸዋለሁ። ዘመኑ ዘመነ ግርምቢጥ የላዩ ወደ ታች የታቹ ውደላይ ሆኗል፣ በአንድ ጽሁፍ ላይ ሐማ ቱማ የተባሉ ጸሀፊ "topsy-turvy" እንዳሉት ነዉ የሆነብን። አቶ ልበላቸዉና አቶ አባኪያ ብርቱካንን ለማሞገስ ሲሉ ሌሎችን ሲያጣጥሉ የጫሩትን በመጠኑ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። አቶ አባኪያ ምን ይሉናል

"ብርቱካን፤ እነሆ ሌላ ታሪካዊ ቅጽበት መጣ። ታስሮ የሟሟ የለም። ቴዲም አልሟሟ። ዶ/ር ታዬም። ታምራትም እንዲሁ። አሁን ያ ታዬ እዚያው እንደታሰረ ቢቀር ይሻለው ነበር እዚህ ከሚርመጠመጥ"

ተመልከቱት የዘመኑን ፖለቲካ፤ ብርቱካንን ለማሞገስ ሲባል ብቻ በደምና ባጥንቱ ያስመሰከረዉን ዶር ታየን ከዚህ ከምናየዉ እንደታሰረ ሞቶ ቀርቶ ቢሆን ነዉ የሚሉን፤ እንዲህ ያለ ዘረኝነት የተጠናወተዉ አባባል ባሁኑ ጊዜ ያስፈልጋል? ለመሆኑ የዶር ታየ እስር ቤት ገብቶ መቅረት ማንን ነዉ የሚረዳዉ? ይህንን ለአንባብያን ነዉ የምተወዉ። የሚከተለዉ ደግሞ እራሴን ነዉ ያዞረዉ ከቴሌቪዝን ላይ የሚለፈልፈዉ ቀጣፊዉ ቤኒ ሂን የሚሉት ቄስ ነኝ ባይ መናፍቅ የጻፈው ነዉ የመሰለኝ።

"የዛሬ ሁለት ሺህ አንድ ዓመት አካባቢም እንዲህ ያለ ተመሳሳይ ጥያቄ በእስራኤለ ውስጥ ተነስቶ ነበር። ዛሬም ሰኔና ሰኞ ተገናኝተዋል። እነሆ ብርቱካን ሚደቅሳ የዛሬ ሁለት ሺህ አንድ ዓመት አካባቢ ትንሽቷ፣ አልባሌዋ፣ የተናቀችው ቤተልሄም የተጋፈጠችው ጥያቄ ከፊቷ ተደቀነባት። ቃል በቃል አላስታውሰውም። በከፊል ግን እንዲህ ነው። ክርስቶስ የሚወለድ ሰሞን፤ በእውኑ አንቺ የኤፍራታዋ ቤተልሄም ከሌሎች የይሁዳ ነገዶች ታንሻለሽን? ነገር ግን የእስራኤል ንጉስ የሚሆን ካነቺ ይወለዳል አይነት ነገር። ቤተልሄምም አላነሰችም። እንዲያውም ልቃ ተገኘች እንጂ። የክርስቲያኖች ንጉስ፤ የክርስትናቸው ማእዘን የሆነው ክርስቶስ ተወለደባት። ብርቱካን ያ የንግስትነት ቅጽበት አምልጧት ነበር። አሁን ተመልሶ መጥቷል። ሰሞኑን ቴዲ አፍሮንና ሌሎች የህሊና እስረኞችን ልናስብ ላይ ታች እያልን ነው። ቴዲ አፍሮ የብርቱካንን ያህል ስለኢትዮጵያዊያን ተሟግቶ አይደለም። እንዲያውም የተወሰነውን ኢትዮጵያዊ አጀንዳ እኛ ጫንበት እንጂ። ሀሳቡም እቅዱም የነበረው አይመስለኝም። እንዲያ ከሆነ፤ በእውኑ ብርቱካን ከቴዲ አፍሮ፣ ከአጼ ቴዎድሮስስ ቢሆን ታንሳለችን? እስካሁን ታንሳለች። አጼ ቴዎድሮስ ግን የሰሩት የሰሩትን ብቻ ነው። ከዚህ በኋላ ሊጨምሩ የሚችሉት አንድም ነገር የላቸው። እነሆ ብርቱካን ከነሱ ሁሉ የምትበልጥበትና ከነኦውንግ

ሳን ሱ ኪ፣ ከነማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ከነማንዴላ፣ ከነጋንዲ ተርታ የምትሰለፍበት ቅጽበት መጥቷል።
"

ምንድን ነው አቶ አባኪያ የሚሉን? ክርስቶስ እንደገና ከብርቱካን ይወለድ ይሆናልና እሷን እስክትወልድ እንጠብቅ ነው? አልሰሙ እንድሆን ለአቶ አባኪያ የምነግራቸው የምስራች ቢኖር ብርቱካን ልጅ ወልዳለች የልጅ አባቷም ዎያኔ ነው። ውደተነሳሁበት ቁም ነገር ልመለስና ብርቱካንን ከቴዲ አፍሮ ስናወዳድር አቶ አባኪያ እንዳሉት ሳይሆን ቴዲ ለኢትዮጵያ እርሳቸው ከሚያከብሯት ብርቱካን የበለጠ ተሟግቷል የታሰረም በዛው ነው። ቴዲ በዘፈኖቹ ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ለፏል። እነአላሙዲ በገንዘብ ሊገዙት ሲሉ አሻፈረኝ ብሏል፤ አዲስ አበባን ጥሎ በሚሊኒየም በአል ጊዜ ዘር ሳይቆጥር ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ላዝናና ብሎ ጅማ ሄዶ አመት በአሉን ከኦሮሞ ወገኖቻችን ጋር አሳልፏል። የአቶ አባኪያ ብርቱካን በዛን ጊዜ ምን ትሰራ ነበር? ያዲስ አበባን ወጣት ከመንገድ ለዎያኔ አስጨፍጭፋ የሙት ዘመዶቻቸውን እግዚአብሄር ያጽናችሁ ሳትል ወደ አሜሪካ በመብረር ከአንገቷ ጉንጉን አበባ እየደረደርች ድርጂት በማፍረስ ተሰማርታ የወያኔንና የፈረንጆችን ስራ ታከናውን ነበር። አቶ አባኪያ እባክዎ ይንገሩን ማነው ኢትዮጵያዊው? ስለ አጼ ተውድሮስ የጻፋትን ሳነብ ከመሳቅ በቀር ሌላ ማለትም አያስፈልግም ነበር። ለአቶ አባኪያ ትንሽ የምላቸው ቢኖር አድኖ የሚበላን አንበሳ የመንደር ትራፊ ወተት ለምና ከምትኖር ድመት ጋር የሚያወዳድር ጤነኛ ሰው ባለመሆኑ እራሱን ያስገምታል ነው። አለም ያደነቀውን መይሳው ካሳ ከሰራው ይልቅ ብርቱካን የሰራችው ይበልጣል ነው የሚሉን? መቸም ይህንን የማወዳደር ቀሻሻ ስራ እኔው ልረከበውና ነካ ነካ ላድርገው። ይህንንም ስላደረግኩ ያጼ ቴዎድሮስን አጽም ይቅርታ እየጠየቅኩ ነው። መይሳው ካሳ ንጉሶቹ በየቦታው የኢትዮጵያን ህዝብ ሲያሰቃዩ አይቶ ሸፍቶ ገበሬውን አስተባብሮ ኢያንዳንዱን በዝባዥ ዎግቶ አጥቅቶ ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ያስቀመጠልን መሪ ነበር። ለዚህም የመጀመሪያው አብዮተኛ መሪ ነው፤ አብዮት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከተረዱት። የርስዎ ብርቱካን ግን ይግረማችሁ ብላ በአማሮች ስም ትግሬዎችን ይቅርታ ጠይቃለች አማሮች ምን እንደበደሉ ግን እስካሁን መልስ አላገኙም። ይህ መከፋፈል እንጅ አንድ ማድረግ አይደለም። አቶ አባኪያ ኢትዮጵያዊው ማነው? አጼ ቴዎድሮስ መለማመጥ አያውቁም ነበር፤ በርሳቸው ጊዜ በሃገራቸው በኢትዮጵያ ቀልድ አይሞከርምም፤ የፈረንጅ አምባሳደር ነኝ ብሎ ወዲያ ወዲህ ማለት አልነበረም፤ ለዛም ነው እንግሊዞችን እስር ቤት የጨመሯቸው። የኢትዮጵያን ህዝብ ነጻ አውጭ ነች የሚሉን ወይዘሮ ብርቱካን ግን ውሏቸው በየአምባሲው ነው፤ ምሳም እራትም የሚበሉ ከዛ ነው፤ ትዕዛዝ የሚቀበሉም ከዛው ነው፤ ገንዘብ የሚነዛውም ከዛው ነው። አጼ ተዎድሮስ አንኳንና የፈረንጅ መጤ ቄስ ይቅርና ሀገር ቤት የተፈጠሩትን እንኳ ስነ ስራት ያስያዙ ናቸው። በሳቸው ጊዜ ካቶሊክ ፕሮቴንስታንት እያሉ እየገቡ አገሪቱን የቅኝ ገዝዎች መፈንጫ እንድትሆን አልፈቀዱም፤ ማንም ትርው እንዳይል ነው ያደረጉት። እንኳንና ለኢትዮጵያ ሱዳንን ሊወር የመጣን አረብ ሁሉ ሲያባርሩ ነው የኖሩት። አጼ ቴዎድሮስ ከኢትዮጵያዊነታቸውም በላይ አፍሪካዊነታቸውን ተረድተው ሌሎችን አገሮች የረዱ ነበሩ። ወይዘሮ ብርቱካን እንኳን የሀገሯን ባህል መጠበቅ ይቅርና መጤ ሐይማኖት ለማስፋፋት ዶላር ተሸክማ የምትቀሰቅስ መታወቂያ የያዘች ሙሉ አባል ናት፤ ያን እንድታስፋፋም ከውጭ የሚለገሳት ገንዘብ ብዙ ነው። አቶ አባኪያ ኢትዮጵያዊው ማነው? አጼ ቴዎድሮስ ለጠላት እጃቸን አልሰጥም ብለው እራሳቸውን ሰውተው ኩራትንና ጀግንነትን ያስተማሩን መሪ ናቸው። መቸም በዘመኑ የአራዳና የፋራ ፖለቲካ አካሄድ እራሳቸውን የገደሉ ጤባ ፋራ ስለሆኑ ነው እንዳይሉኝ። የርስዎ ብርቱካን ግን አስፈራሩኝ ብላ እስካጃቢዎቿ ትጨሃለች፤ አቤት አራዳነት ያውም ለማስመሰሉ ማስጠንቀቅያ። አቶ አባኪያ አሁንም መልሼ ልጠይቅዎ፤ ኢትዮጵያዊው ማነው? ድህነታችን ስለበደለን ፈረንጆቹ እኛኑ በኛው እያጠፉን ነው። አቶ አባኪያ እባክዎ አያናግሩኝ ሆዴ ባዶ እንዳይቀር እንዴት ተብሎ ነው ብርቱካን ከነ አጼ ቴዎድሮስ "የምትበልጥበትና ከነኦውንግ ሳን ሱ ኪ፣ ከነማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ከነማንዴላ፣ ከነጋንዲ ተርታ የምትሰለፍበት" እነ አጼ ተዎድሮስ ከነዚህ ከጠቀሱዋቸው ሰዎች ያንሳሉ ማለትዎ እኮ ነው፤ ወይ ዘመን፤ ዘመነ ክህደት፤ ዘመነ ባንዳነት። ለነገሩ ሀገር ከተሸጠ ባህላችን ከደቀቀ ሀይማኖታችን ከተነጠቅን እኮ ቆየት ብሏል። አቶ አባኪያ በዘመኑ ነው እንጅ

በርስዎ እኮ አናዝንም ፤ የወያኔው ጳጳስ ነኝ ባዩ አቶ ገ/መድህን ራቁቷን የምትደንስ የፈረንጅ ዘፋኝን የቤተ መቅደስ ጥላ ይዞ ሲያጅብ እኮ ነው ወይ ዘመን ያልነው። መናፍቃን በነብርቱካን እየተመሩ ኢትዮጵያ ሃይማኖት እስካሁን የላትም እኛን ተከተሉ ይኸው ገንዘቡ እያሉ ባህላችን አርክሰው የነርሱን የረከሰ ባህል ሰያስፋፉ እያየን እኮ ነው ወይ ዘመኑ ያልነው። እርስዎስ የድርሻወን ይዘው ኢትዮጵያ ከብርቱካን ሌላ መሪ አይታ አትውቅም ሲሉን ምን እንላለን ወይ ዘመኑ ካልሆነ በቀር። አቶ አባኪያ እንደርስዎና እንደ ፈረንጅ አምላኪ መሪዎ ብርቱካን ሚደቅሳ ሳይሆን ለንደኛ አይነቱ ኢትዮጵያዊያን ከቴዎድሮስ የበለጠ መሪ የለንም ለውደፊቱም የሚኖር አይመስለንም። ስለዚህ ከመጻፍዎ በፊት ያንቡ፤ ታሪክን ይመርምሩ ዱባና ቅል ሰራቸው እየቀል ተብሏል በነፍጠኞች ቋንቋ ማለቴ ነው። ብርቱካንን ያለ መሰላል ከላይ ለመስቀል ሲሉ ብቻ ጀግኖቻችን ወደታች ፈረንጆችን ወደላይ አድርገው ሲያስቀምጡ፤ እርሷንም ያላቅሟ የማትችለው ውድድር ውስጥ እየከተቱ አያሳፍሯት፤ አያስፈሯት፤ ውድድሩን አትችለውምና ያቅሟን ያስይዟት ካቅሟ በላይ አይጫኗት።

ምንም የማስምሰል ደባ ቢካሀድብንም ግራም ነፈሰ ቀኝ ወያኔ እውነተኛ ጠላቱን ለይቶ ያውቃል። የሚያድነውም፤ የሚገለውም ብርቱካንን ሳይሆን እውነተኛ ኢትዮጵያውያንን ለኢትዮጵያ በሀቅ ቆመው የሚታገሉትን ነው። ይህም በግልጽ የምናውቀው ሀቅ ከፊታችን ተደቅኗል ኢትዮጵያዊያንም እየተመለከቱት ነው፤ ይኸውም ብርቱካን የዎያኔ ጠላት በፍጹም ልትሆን አትችልም፤ አይደለችምም። ይህ ሁሉ ጫጫታ የመጣው የብርቱካን ደጋፊ ማነስ ስለታየ ብቻና የሚቀጥለው አስመሳይ ምርጫ ባቋራጭ ስለደረሰ ብቻ ነው። ለዚያውም እራሷ የመረጠችው ወያኔን በመደገፍ የተሰለፈችበት አላማ ስለሆነ ነው፤ ያው እንደ ልደቱ አያሌው አካሄድ ማለት ነው። ብርቱካን የኢትዮጵያ ህዝብ የሰጣትን አደራ በልታ የፈረንጅ ቄሶችና የጅ አዙር ቅኝ ገዥዎች የሰጧትን የቤት ስራ ነው የምትሰራው። የሚገርመው ወያኔ ህቀኛ ታጋይቱን መሶብወርቅን አስሯል። ታጋይ እስርን አይፈራም ያንንም እያየን ነው መሶብዎርቅ በምታምንበት ስራዋ ለህዝብ ብላ ገብታለች። የሚገርመው ግን የብርቱካንና አሽከሮቿ መጨሀ ነው። አቶ አባኪያ የምጣዱ ሳለ የእንቅቡ ተንጣጣ ሲባል ሰምተው ያውቃሉ ወይስ የነፍጠኛ ቋንቋ ብለው ትተውት ነው? እውነት መቸ ነው የምትጎላው? ህዝብ መረዳት ያለበት ይህ ሁሉ ጫጫታ ለማስመሰል የተሰራ የወያኔና የነብርቱካን ስራ ነው። ያማ ባይሆን ብርቱካን ከአጼ ቴዎድሮስ ትበልጣለች ኢንዲያውም እየሱሥን ትዎልድልናለች አይነት አባባል መሰለኝ ነገሩ፤ አንባልም ነበር። ምንኛ ቢንቁን ነው እኒህ ወያኔዎች የኢትዮጵያ ህዝብ እንደነርሱ የተፋቸውን ሰወች መልሰው ሊያበሉት የሚፈልጉት? ይህ ሁሉ ጫጫታ ባሁኑ የጉድ ዘመን ለፈረንጅ ያላጎበደደ፤ ባህሉንም ሆነ ሃይማኖቱን እስከነ ሀገሩ ያልሸጠ፤ ያልከዳና ለፍርፋሪ ያላደረ ጀግና የማይባልበት በተቃራኒው የሚሰራና በክህደት የተሰማራ የሚከበርበት በመሆኑ ነው። እርስዎ እንዲያውቁት የምፈልገው ግን ብርቱካንን በመደገፍዎ መብትዎ የተጠበቀ በመሆኑ ቅሬታ ያለው ሰው አይኖርም። ነገር ግን ቅሬታው በጥያቄ መልክ ከደበላለቁት ላይ ነው። ስለዚህ አቶ አባኪያ ለጠየቁት ጥያቄ "በእውኑ ብርቱካን ከቴዲ አፍሮ ታንሳለችን? ከአጼ ቴዎድሮስስ ቢሆን?" መልሱ እንደገና ዱባና ቅል ሰራቸው እየቀል ተብሏል። በሌላ አነጋገር ደግሞ ጋኖቹ አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ ተብሏል፤ በነፍጠኞች ቋንቋ ማለቴ ነው።

በደህና ይክረሙ።

ጋሻ ቀለሙ

gashakelemu@yahoo.com